EVERY CASUALTY COUNTS

# የተጎጂ አመዘጋገብ መመዘኛዎች አጭር መግለጫ

ማውጫ


የተጎጂ አመዘጋገብ መመዘኛዎች አጭር መግለጫ 2

የተጎጂዎች አመዘጋገብ መርሆዎች 3

1. ምንም ዓይነት ጉዳት አለማድረስ 3
2. ግልጽነት 3
3. አካታችነት 3
4. ወጥነት 3
5. ኃላፊነት 3

ለተጎጂ መዝጋቢዎች መሠረታዊ የመረጃ አሰባሰብ ግቦች 4

የተጎጂ አመዘጋገብ መመዘኛዎች 5

1. ተቋማዊ ግልጸኝነት 5
2. የመረጃ ማሰባሰቢያ ስልቶች 5
3. ትርጉሞች እና ምድቦች 6
4. ደህንነት 6
5. የተጎጂዎች ምዝገባ መረጃዎችን ማሳተም 7

# የተጎጂ አመዘጋገብ መመዘኛዎች አጭር መግለጫ

*ይህ ሰነድ የተጎጂ ሁኔታን ለመመዝገብ የወጡ መመዘኛዎች አጭር፣ ቀላልና ተደራሽ የሆነ አጭር ማጠቃለያ ነው።* የዚህ ሰነድ ሙሉ ክፍል በ፡ www.everycasualty.org ላይ ይገኛል።

እነዚህ የተጎጂ ምዝገባ መመዘኛዎች የተዘጋጁት የእያንዳንዱ ተጎጂ ህይወት ዋጋ አለው በተባለው የተጎጂ መዝጋቢዎች የትስስር መረብ አማካኝነት ሲሆን ምርጥ ተሞክሮዎችን ለማስተዋወቅ፣ ወጥነት ያለው አሠራርን ለማበረታታት እንዲሁም የተጎጂ መዝጋቢዎች የሥራ ውጤት በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማስቻል ነው። ሆኖም ግን የሥራ መመሪያ ሆነው እንዲያገለግሉ ዓላማ የተደረጉ አይደሉም። ይልቁንስ የመመዘኛዎቹ ዓላማ የተጎጂ መዝጋቢዎች የመልካም አሰራር ልምድን አስፈላጊ ገጽታዎችን ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ ለማበረታታት እና እነዚህንም በሚሰሩት የተጎጂዎች ምዝገባ ፕሮጀክት ውስጥ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው ለማስገንዘብ ነው።

በተጨማሪም ፣ እነዚህ መመዘኛዎች የተጎጂ መረጃ በቀላሉ ጥቅም ላይ ለማዋል እና ለማጋራት እንዲቻል፣ የተጎጂ ምዝገባ ባለሙያዎችን ለማገዝ ዓላማ ያደረጉ ናቸው። የተጎጂ መረጃ ተጠቃሚዎች ከተለያዩ ምንጮች በኩል የቀረቡ የተጎጂ መረጃዎችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው እና እንደሌለባቸው እንዲሁም በምን መልኩ መጠቀም እንዳለባቸው የሚረዱ ተጨባጭ እና ሊለኩ የሚችሉ መስፈርቶችን ያቀርባሉ።

የመመዘኛዎቹን ተደራሽነት እና አገልግሎትን ለማስፋት፣ ይህ አጭር መግለጫ ለነባር የተጎጂዎች መዝጋቢዎች እና ወደፊት የተጎጂ መዝጋቢ ሊሆኑ ለሚችሉ ሠዎች በጣም አስፈላጊ በሆኑ በበርካታ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። ለተጨማሪ መረጃ እና ግብዓት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገኙ ማንኛውም ዓይነት የአደጋ ሰለባዎችን አግኝተው ያነጋግሩ።

# የተጎጂዎች አመዘጋገብ መርሆዎች

መመዘኛዎቹ በተዘጋጁበት ወቅት በአምስት ዋና ዋና መርሆዎች ላይ ስምምነት ተደርሷል። በዚህ ክፍል የቀረቡት ሁሉም መመዘኛዎች እነዚህን መርሆዎች መሰረት ያደረጉ ናቸው፣ በመሆኑም በማንኛውም የፕሮጀክት ሥራ ሂደት ተግባር ላይ መዋል አለባቸው።

## 1. ምንም ዓይነት ጉዳት አለማድረስ

ከህክምና ሞያ የሥነምግባር የመነጨው፣ በሕይወት ባላቸው ነገሮች ላይ ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ ማድረግ የሚለው መሰረታዊ የአመዘጋገብ መርህ ከሌሎቹ ቀሪ አራት መርሆዎች የሚልቅ ታላቅ መርህ ነው። ይህ መርህ፣ መረጃ መሰብሰብ ጀምሮ እስከ ደህንነት ፖሊሲዎች እና የመረጃ ህትመት ድረስ ባሉ በሁሉም የተጎጂ አመዘጋገብ ገጽታዎች ወስጥ ተፈጻሚ ነው፡፡

## 2. ግልጽነት

የተጎጂ መዝጋቢዎች ፣ተቋማዊ አወቃቀርን፣ የመረጃ አሰባሰብ ስልቶችን እንዲሁም የሠራተኞችን፣ የምስክሮችን እና የመረጃ ደህንነት ፖሊሲዎችን ጨምሮ በተቻለ መጠን በሁሉም የሥራ እንቅስቃሴዎች ግልጽነትን የተላበሱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ግልጽነት በመረጃው ላይ ተዓማኒነት ይጨምራል፣ መረጃው በትክክል እንዲተረጎም ይረዳል፣ እንዲሁም ጠቃሚ የምርመራ ሂደቶችን ያበረታታል፡፡

## 3. አካታችነት

መዝጋቢዎች የግድ ከፖለቲካ ገለልተኛ እንዲሆኑ አይጠበቅም ፣ ነገር ግን ሁሉም ወገኖች በእኩል የሚመለከቱ አተረጎሞችን በመጠቀም የፕሮጀክቱ የትግበራ ወሰን እስከሆነ ድረስ ሁሉንም ዓይነት ክስተቶች እና የጉዳት ዓይነቶችን ለማካተት የግድ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ የተጎጂ መዝጋቢዎች በመዝገባቸው ውስጥ ያላካተቱት መረጃ ካለ ምን ዓይነት መረጃ እንደሆነ እና በምን ምክንያት እንደሆነ በግልጽ መጥቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ለምሳሌ፣ የዘጋቢውን የፖለቲካ ወይም የማኅበረሰብ አባልነት ከሚቃወሙ ማኅበረሰቦች በኩል መረጃ ለመሰብሰብ ያጋጠሙ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ሊጨምር ይችላል፡፡

## 4. ወጥነት

በተለይ ከመረጃ መሰብሰቢያ እና ትንተና ስልቶች ጋር በተያያዘ ወጥነት ያለው አሰራር እንዲኖር ማድረግ የተጎጂ መዝገቦች ከጊዜ እና ከቦታ አንጻር ትርጉም ያለው ንጽጽር ለማድረግ እንዲያስችሉ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ በተለዋዋጭ ውጫዊ ሁኔታዎች የተነሳ የመረጃ ማሰባሰቢያ ስልቶች የሚቀየሩ ከሆነ፣የመረጃ ወጥነትን ለማረጋገጥ በጥንቃቄ መመርመር ፣ እንዲሁም በግልጽ መቀመጥ አለባቸው፡፡

## 5. ኃላፊነት

የተጎጂ መዝጋቢዎች የመረጃ ምንጮቻቸውን ጨምሮ የሥራ ባልደረቦቻቸውን እናጉዳት የደረሰባቸው ወይም በሰራው ተሳታፊ አካላት ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት ሃላፊነት በተሞላበት መንገድ መሆን አለበት፡፡ የመረጃ ሰጭዎችን እና ተጠቃሚዎችን አመኔታን ለማሳደግ እንዲቻል የሃላፊነት ተግባር በግልጽ መታየት አለበት፡፡

# ለተጎጂ መዝጋቢዎች መሠረታዊ የመረጃ አሰባሰብ ግቦች

የተጎጂ መዝጋቢዎች በፕሮጀክቶቻቸው ዝርዝር ግቦች መሰረት የመረጃ አሰባሰብ መስፈርቶቻቸውን ያዘጋጃሉ፡፡ ሆኖም ግን ሁሉም የተጎጂ መዝጋቢዎች ሊያካትቷቸው የሚገቡ አነስተኛ ጥቅል መሠረታዊ መረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡-

| **መሠረታዊ የመረጃ አሰባሰብ ግቦች** | |
|---|---|
| **ቦታ** | ስለቦታው በከፍተኛ ደረጃ በዝርዝር የሚገኝ መረጃን መመዝገብ፣ ለምሳሌ የከተማውን ወይም የመንደሩን ስም ወይም የሚቻል ከሆነ ሙሉ የጂፒኤስ አመልካች ነጥቦችን መመዝገብ። |
| **ቀን/ሠዓት** | የሚታወቅ ከሆነ ቀንና ሠዓትን ጨምሮ በከፍተኛ ደረጃ በዝርዝር የሚገኝ መረጃን መመዝገብ፡፡ |
| **የመረጃ ምን ጮች** | እንደ የዜና ዘገባዎችን፣ ኦፊሴያላዊ ሠነዶችን፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ግብዓቶችን፣ ወይም የእማኝ ምስክርነቶችን የመሳሰሉ የመረጃ ምንጭ ምድቦችን መመዝገብ። የመረጃ ምንጮች ከተጎጂ መዝገቦች ጋር ተያይዘው እና ተጠብቀው መቆየት አለባቸው።  እንደ የምስክርነት ቃል የመሳሰሉ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው የመረጃ ምንጮች ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል። |
| **የተጎጂዎች ቁጥር** | በአንድ ተለይቶ በታወቀ ክስተት የተገደሉ ሠዎችን ማንነት ለመለየት የሚያስችል መረጃ ካልተገኘ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ማግኘት እስከሚቻል ድረስ የተጎጅዎችን ቁጥር እንደ ጊዜያዊ እርምጃ መዝግቦ መያዝ። |
| **ስም** | የአካባቢያዊ የስም አወጣጥ የልምድ ዕውቀትን በመጠቀም የእያንዳንዱን ተጎጂ ስም ይመዝግቡ። አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ አንድ ግለሰብ የሚጠራባቸው የተለያዩ ስሞችን ማካተትዎን እርግጠኛ ይሁኑ (ለምሳሌ፣ የብዕር ስም ወይም ቅጽል ስሞችን)። |
| **ዕድሜ** | በሞተበት ወይም በጠፉበት ወቅት የእያንዳንዱን ተጎጅ የትውልድ ቀን፣ ወይም ዕድሜውን መዝግበው ይያዙ። ይህን መረጃ ማግኘት ካልተቻለ፣ ግልጽ እና ወጥ የሆነ መስፈርት በመጠቀም ተጎጅው ህፃን ወይም አዋቂ መሆኑን ይመዝግቡ።  እንዲሁም ህጻን፣ ጨቅላ ህጻን፣ ጎረምሳ፣ ወይም ሽማግሌ የመሳሰሉ ተጨማሪ መለያ ምደባዎች ጥቅም ላይ ከዋሉ ወጥነት ባለው ሁኔታ መሆን ይኖርባቸዋል። |
| **ጾታ/ስርዓ ተ ጾታ** | በተቻለ መጠን የእያንዳንዱን ግለሰብ ጾታ/ስርዓተ ጾታን መዝግበው ይያዙ። |
| **የአሟሟት ዝርዝር መረጃ** | ይህን መረጃ በተለያየ መንገድ ማደራጀት ይቻላል፣ ለምሳሌ፣ በጦር መሳሪያ፣ የሞቱ ምክንያት የህክምና ወይም የግጭቱ ዝርዝር መግለጫ። |
| **የድርጊቱ ተዋናዮች** | በግጭቱ ውስጥ የተገኙ አካላት ወይም ቡድኖች ወይም ለግጭቱ ሃላፊነት የወሰዱ ግለሰቦችን ጨምሮ በግጭቱ ተሳትፈዋል የተባሉ አካላትን እና/ወይም ግለሰቦችን ይመዝግቡ። |

# የተጎጂ አመዘጋገብ መመዘኛዎች

## 1. ተቋማዊ ግልጽኝነት

የተጎጂ መዝጋቢዎች አዘውትረው:-

- የምዝገባ ተልዕኮአቸውን እና ተነሳሽነታቸውን በተመለከተ ግልጸኝነት ይኖራቸዋል።
- የመረጃ አሰባሰብ ስልቶችቻቸውን በተመለከተ ግልጽ እና ለህዝብ ተደራሽ የሆነ መረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

የተጎጂ መዝጋቢዎች የሚከተሉትን ጉዳዮች ለመፈጸም ጥረት ማድረግ አለባቸው:-

- አካታች የሆነ ምዝገባ ለማከናወን ሊኖራቸው በሚችለው ቁርጠኝነት ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥር የሚችል ፖለቲካዊ ወይም ሌሎች የቡድን ትስስሮቻቸውን በተመለከተ መረጃ ይሰጣሉ።
- የሚሰሩበት ተቋም መዋቅርን ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ግልጽ እና ተደራሽ ያደርጋሉ።
- ለጋሽ ድርጅቶችን በሚመለከት ግልጽ እና ለህዝብ ተደራሽ የሆነ መረጃ ያቀርባሉ።

## 2. የመረጃ ማሰባሰቢያ ስልቶች

የተጎጂ መዝጋቢዎች አዘውትረው:-

- የሰነድ ማስረጃ እና የምስክርነት ቃሎችን በሚመለከት ግልጽ የሆነ የአሰራር መንገድ ይኖራቸዋል።
- የሠዎችን አስተያየት እና ነፃነት በማይገድብ መልኩ ወጥነት ያለው እና በደንብ የተደራጀ የመረጃ ትንተና ስርዓት ይኖራቸዋል።
- የተለዩ መረጃዎችን በተጠና ሁኔታ ይመዘግባሉ።
- የተሰበሰበውን መረጃ ለማጠናከር እና ለመፈተሽ የሚረዱ ሂደቶች ይኖራቸዋል።
- በመረጃ ምንጮች መካከል ሊከሰቱ የሚችሉ አለመጣጣሞችን ለማስታረቅ የሚያስችል የአሠራር ስርዓት ይኖራቸዋል።
- ድግግሞሽ የሚስተዋልባቸው ምዝገባዎችን ለማስቀረት ወይም ለመፍታት የሚረዱ መንገዶች አላቸው።

የተጎጂ መዝጋቢዎች የሚከተሉትን ጉዳዮች ለመፈጸም ጥረት ማድረግ አለባቸው:-

- በተቻለ መጠን ለእያንዳንዱ መዝገብ ነጻ የሆኑ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን ይጠቀማሉ።
- የመረጃ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ በዙሪያቸው ያሉ ሰዎችን ያውቃሉ እንዲሁም ጠንካራ እና ደካማ ጎናቸውን ይለያሉ ።
- የእያንዳንዱን የመረጃ ምንጭ የተዓማኒነት ደረጃ መመዘኛን ለመጠቀም እንዲሁም ለግምገማ ክፍት ናቸው።
- ምንም እንኳ ሊገኝ የሚችለው መረጃ ትንሽ ቢሆንም፣ ጠቃሚ መረጃ ሊሰጥ የሚችል ማንኛውንም የመረጃ ምንጭ ውድቅ አያደርጉም።
- እያንዳንዱን ጠቃሚ መረጃ በአግባቡ ያስቀምጣሉ ።

- ገለልተኛ በሆኑ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም መረጃዎችን ለማጠናከር ግብ ያደርጋሉ።
- ወጥነት ያለው መረጃ ወደ መረጃ አገባብ የሚያረጋግጡ አሰራሮችን ይዘረጋሉ።
- ወደ መረጃ ቋት የሚገቡ ሁሉም መረጃዎች ለዕርማት እንዲሁም አዳዲስ መረጃዎችን ለመጨመር በሚያስችል ሁኔታ ክፍት ያደርጋሉ።
- የሥራ ሂደቱን ለማቃለል እና ሊፈጠሩ የሚችሉ ስህተቶችን ለመቀነስ የተጎጂዎች የአመዘጋገብ ሂደትን በተለያዩ ሠዎች እንዲከወን ያከፋፍላሉ።
- በእያንዳንዱ የጉዳት ክስተት/ግለሰብ ማረጋገጫ ከመስጠት በፊት የሥራ ባልደረቦች አንዱ የሌላኛውን የመረጃ መገምገም እንደሚችል ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባሉ።

## 3. ትርጉሞች እና ምድቦች

የተጎጂ መዝጋቢዎች አዘውትረው:-

- በግልጽ ማብራሪያ የሚሰጡ፣ ግልጽ አካታች እና አግላይ የሆኑትን የሚለዩ መስፈርቶችን ያዘጋጃሉ።
- ከአውዳቸው እና ዓላማቸው ጋር የሚዛመዱ ትርጉሞችን እና ምድቦችን ይመርጣሉ።
- ከተጎጂ ምዝገባ በፊት የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ነጥቦችን፣ ምድቦችን፣ እና ትርጉሞችን ይወስናሉ እንዲሁም በምዝገባ ሂደቱ ወቅት ወጥነት ባለው መንገድ ተግባራዊ ያደርጋሉ።

የተጎጂ መዝጋቢዎች የሚከተሉትን ጉዳዮች ለመፈጸም ጥረት ማድረግ አለባቸው:-

- ሁኔታዎች የሚፈቅዱ ከሆነ አንድን መረጃ "ያልተረጋገጠ" ወይም "ጊዜያዊ" ብሎ ለመለየት አማራጭ ይኖራቸዋል።
- የመረጃ ቋታቸውን በሚያዘጋጁበት ጊዜ ከምደባ ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ያስገባሉ።
- ተለይተው ያልታወቁ ግለሰቦችን ሞት በተመለከተ በተቻለ መጠን ዝርዝር ሁኔታዎችን ይመዘግባሉ።
- ተለይተው ያልታወቁ የጉዳት ሰለባዎችን ዕጣ ፈንታ ግልጽ ለማድረግ፣ የጠፉ ግለሰቦችን በተመለከተ የተለየ የመረጃ ቋት ያዘጋጃሉ እና/ወይም ያጠናቅራሉ።

## 4. ደህንነት

የተጎጂ መዝጋቢዎች አዘውትረው:-

- ስጋቶች ሊቀያየሩ እንደሚችሉ እና ከእያንዳንዱ የተጎጂ ምዝገባ ሂደቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ልዩ ስጋቶችን መለየት እንደሚያስፈልግ ግንዛቤ አላቸው።
- የሚሰጡት መረጃ ለምን ዓላማ ሊውል እንደሚችል በዝርዝር በማሳወቅ አግባብነት ካላቸው ምስክሮች በመረጃ ላይ የተመሰረተ የስምምነት ፈቃድ ይጠይቃሉ።
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚስጥራዊነትን እና ልዩነትን በሚጠይቅ መልኩ በሁሉም የሥራ ባልደረቦች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን በጽሁፍ ወይም በቃል ውል አማካይነት በግልጽ ያስቀምጣሉ።
- እነሱን ለመጠበቅ በቦታው የሚገኙ የደህንነት እርምጃዎችን በተመለከተ በሁሉም ሠራተኞች ዘንድ ግንዛቤው መኖሩን፣ መስማማታቸውን እና ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ።

- ስልጠናዎችን ጨምሮ እንደአስፈላጊነቱ የደህንነት ፕሮቶኮሎችን ያዘጋጃሉ እንዲሁም ለሠራተኞች ያቀርባሉ።
- ለሰራተኞቻቸው የስነ-ልቦና ድጋፍ ተደራሽነትን ደረጃን ዋስትናን ያረጋግጣሉ።
- መረጃ መሰብሰብ ከመጀመራቸው በፊት የመረጃ ማከማቻ ዕቅድ እና የመረጃ ቅጅ አያያዝ መመሪያዎች እንዲኖር ያደርጋሉ።
- የመረጃ ጥበቃ ህጎችን ጨምሮ ሌሎች የመረጃ ደህንነት ጉዳዮችን በሚመለከት ህጋዊ፣ ቴክኖሎጂያዊ እና ሰብዓዊ ገዳዩችን ከግምት ውስጥ ያስገባሉ ።
- መረጃን ለሌሎች አጋር አካላት በሚያጋሩበት ጊዜ የመረጃ ደህንነትን ጥበቃ መስፈርቶችን በግልጽ ያስቀምጣሉ።
- የመረጃ ጥሰት ሊያጋጥም እንደሚችል በመገመት ቀድሞ ይዘጋጃሉ።
- የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች የመረጃ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች የሚያሟሉ መሆን አለመሆናቸውን በጥልቀት ይፈትሻሉ።

የተጎጂ መዝጋቢዎች የሚከተሉትን ለመከወን መትጋት አለባቸው፡-

- በተጎጂ ምዝገባ እንቅስቃሴ የሚያሳትፏቸውን ሠዎች ደህንነት ለማረጋገጥ የማይቀረጥ የስጋት ግምገማ ማድረግ ይኖርባቸዋል።
- ከሚሰበስቧቸው የመረጃ ዓይነት ጋር ተያይዞ ምን አይነት ስጋት አለ የሚለውን መተንተን አለባቸው።
- የሚፈልጉትን እና ተገቢውን ጥበቃ ሊያደርጉለት የሚችሉትን መረጃ ብቻ መሰብሰብ አለባቸው።
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ምስክሮችን ወደ እነርሱ ለመምራት እንዲቻል፣ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት አካባቢ የሰብዓዊ ዕርዳታ ሰጋሾች እና የሰብዓዊ መብት ድጋፍ የሚያደርጉ ድርጅቶች መኖራቸውን ማወቅ አለባቸው።
- ለማወቅ የሚገባውን ብቻ መሰረት በተቋሙ ወስጥ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው መረጃዎች ለማግኘት የተለያዩ ደረጃዎች ማስቀመጥ አለባቸው።
- ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ መረጃቸውን በምን መልኩ መዝግበው መያዝ እንዳለባቸው ማቀድ።

## 5. የተጎጂዎች ምዝገባ መረጃዎችን ማሳተም

የተጎጂ መዝጋቢዎች አዘውትረው፡-

- እንዲታተሙ የተደረጉ መረጃዎች በበቂ ሁኔታ ያልተጠናቀሩ ከሆኑ ሙሉ በሙሉ ያልተረጋገጡ ስለመሆናቸው ፍንጭ ይሰጣሉ።

የተጎጂ መዝጋቢዎች የሚከተሉትን ለመከወን መትጋት አለባቸው፡-

- ለህትመት መቅረብ ያለበትን መረጃ ሲወስኑ፣መረጃው ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችልባቸው መንገዶች ሁሉ ፣ እንዲሁም ለማን እንደሚጠቅም፣ ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።
- የተለየ መረጃ እንዳይታተም የወሰኑበትን ምክንያቶቻቸውን መለየት አለባቸው።

- የታተሙ መረጃዎችን ከፕሮጀክቱ ዓላማዎች አንጻር ማሰባሰብ፣ ነገር ግን ሁሌም ቢሆን መሰረታዊ የሆነው ዓላማ ለማንኛውም ዓይነት ጉዳት እውቅና መስጠት እና መመዝገብ እንደሆነ መገንዘብ አለባቸው።
- መረጃቸውን ለማስተላለፍ በጣም ውጤታማ የሆኑ መንገዶችን መፈተሽ እና መለየት አለባቸው።
- ምንጊዜም ቢሆን መረጃዎቻቸውን እንቅስቃሴ በሚያደርጉበት አካባቢ በሚነገር ቋንቋ/ዎች በመጠቀም ለህትመት ለማቅረብ መሞከር አለባቸው።
- መረጃዎቻቸውን ጠቃሚ ለሆኑ እና ትኩረት ለተደረገባቸው ታዳሚዎች ለማሳተፍ የተደራሽነት የማዳረስ እንቅስቃሴዎችን መተግበር አለባቸው።
- የሥራ ድግግሞሽን ለማስቀረት እንዲቻል በተቻለ መጠን መረጃዎችን በስፋት ለማሰራጨት ጥረት ማድረግ፣ ነገር ግን እንደ የጉዳዩ መሰጠት የሚፈልጉትን ዝርዝር ደረጃ መወሰን ይችላሉ።